AHRE

Association for Human Rights in Ethiopia

# ከህግ ውጭ የሚደረግ እስር እና ግለሰቦችን መሰወር ሊቆም ይገባል

ስብስብ ለሰብአዊ መብቶች በኢትዮጵያ ባለፉት ጥቂት አመታት የመጣውን የፖለቲካ ለውጥ ተከትሎ በሃገሪቱ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ መሻሻል ሂደት ላይየሰብአዊ መብቶች ተቋማት እናየህግ መሻሻሎች መታየታቸው እንደ በጎየሚነሳ መሆኑን ይገነዘባል። ነገር ግን መንግስት የዜጎችን ደህንነት የመጠበቅ እንዲሁም የሰብአዊ መብቶችን የማክበር፣ የማስከበር እናየማሟላት ግዴታዎቹን በአግባቡ ባለመወጣቱ ምክንያት በየጊዜው እየተፈጸሙ ያሉ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እጅጉን ያሳስቡታል።

ለዚህም በጋዜጠኞች ላይ በተደጋጋሚ የሚደርሰው ከህግ ውጭ እስር፣ መሰወር እንዲሁም ፍርድ ቤት ህግን ተከትሎ አለመቅረብ እና የሰብአዊ መብቶች ተግባራዊነት አፈፃፀም ክፍተት አንዱ ማሳያ ነው ብሎ ያምናል። ሰዎችን በሃይል መሰወር በኢትዮጵያህጎች፣ በፈረመቻቸው አለም አቀፍ ድንጋጌዎች እናአለም አቀፍ የልማድ ህግ (International Customary Law) የተከለከለ ነው። በተጨማሪም በመንግስታቱ ድርጅት ስር በወጡ በሃይል መሰወርን የሚመለከቱ ህጎች፣ አለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች እና የሰብአዊ መብቶች ኮሚቴዎች ውሳኔዎች ፍፁም የተከለከለ (absolutely prohibited) ተግባር ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ በሃይል መሰወር ለሰብአዊ መብቶች መከበር ተግዳሮት የሚሆን ድርጊት ከመሆኑም በላይ በተሰወርው ሰው እና በቤተሰቡ ላይ የሚያደርሰው ሰቆቃ አስከፊ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

በመሆኑም መንግስት ሚያዚያ 23 ቀን 2014 ዓ.ም ከቤቱ ተወስዶ የት እንደገባየማይታወቀውን ጋዜጠኛ ጎበዜ ሲሳይ ለምን፣በማን እንደተወሰደ እና ያለበትን ቦታ እና ሁኔታ በማጣራት እንዲያሳውቅ እንዲሁም ተያያዥ ሰብአዊ መብቶችን የማክበር፣ የማስከበር እና የማሟላት የህግ ግዴታዎቹን እንዲወጣ እንጠይቃለን።

ግንቦት 1/2014 ዓ.ም
አዲስ አበባ

AHRE

Association for Human Rights in Ethiopia

# Illegal Arrests and Disappearances Must End

Association for Human Rights in Ethiopia (AHRE) recognizes the promising legal and institutional reforms undertaken in the wake of the recent political upheaval in Ethiopia. However, due to the government's failure to fulfill its obligations to protect, respect, uphold, and fulfill the human rights of citizens, the ongoing human rights abuses are of great concern.

AHRE believes that the frequent illegal arrests of journalists, their disappearance, inability to enjoy their right to habeas corpus and human rights abuses against them are among others, manifesting the deteriorating human rights condition in the country. Forced disappearances are prohibited under domestic laws of the country, international conventions that it is a party to and international customary laws. In addition, the laws of the United Nations on forced disappearances and the decisions of the International Courts and Human Rights Committees absolutely prohibit forced disappearances. In connection with this, it should be noted that forced disappearance is a challenge to human rights and is a cause for the grave suffering of the missing person and his/her family.

Therefore, we urge the government to immediately release information regarding journalist Gobeze Sisay, who was abducted from his home on May 1, 2022, and to announce why, by whom and where he is being held. Besides we also call upon the government to fulfill its legal obligations of respecting, protecting, and enforcing human rights.

MAY 9/2022
ADDIS ABABA